# የሞተ ፈረስ መደብደብ ወንዝ አያሻግርም

ታሪኩ አባዳማ     የካቲት 2001

ወያኔ ከዘረጋው የጥፋት አሽከላ ፀድተን አገራችን ከገጠማት ፈተና እንድትላቀቅ ለማስቻል ጥበብ እና ብልሀት የተመላበት ፤ ትዕግስት እና መቻቻል የሰፈነበት ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ግብ ላይ ያነጣጠረ ሰፊ የፖለቲካ ሥራ ማከናወን የግድ ነው። የራዕይ ዕጦት የለብንም - ብዙ ህብረ-ብሔር የፖለቲካ ድርጅቶች አሉን ፤ ማርና ወተት ወደሚፈስባት የተስፋይቱ ምድር እናደርሳችኋለን የሚሉ ሙሴዎች ጥቂት አይደሉም።። ያንድ ክልል ጉዳይ ይበልጥ ያሳስበናል የሚሉ የጎጥ ሙሴዎችም ሞልተዋል። በዚያው ልክ በስፋት የተነደፉ ፕሮግራሞች እና መፈክሮች አሉ። ሁሉም ሕዝብ ሕዝብ እያለ ነው።

ይሁንና፣ ሸጋ ፕሮግራም ነድፎ ያንን የሚመጥን አደረጃጀት ፣ ስልት እና ስትራተጂ ካልታከለበት ወረቀቱ ወረቀት - ትግሉ ውሀ ፣ አገሪቱ የጎጠኞች ሰላባ  ፤ የታሰበው ሁሉ መና ሆኖ ይቀራል። ሕዝባዊ ለመሆን ከባዶ ፕሮፖጋንዳ የዘለለ ፣ በሕዝብ ዘላቂ ጥቅም እና ሕልውና ላይ ያነጣጠረ ጎዳና መከተል ያሻል። ብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት በተካሄደው እርምጃ ውስጥ አዎንታዊ የሚባሉ ታሪካዊ ትስስሮችን ይበልጥ ማጎልበት እና ለፖለቲካ ድል መሠረት ሊሆኑ እንዲበቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሕዝብ የስልጣን ምንጭ እና ባለቤት መሆኑን ከልብ ተቀብሎ በዚያ አቅጣጫ መንቀሳቀስ ለሕዝባዊነት የማዕዘን ደንጊያ ነው። በዚህ ረገድ የሕዝብ ሞግዚት ልሆን ይገባኛል የሚል ሳይሆን የሕዝብ ፈቃድ ፈፃሚ ለመሆን ተዘጋጅቻለሁ ብሎ የቆመ ፤ ሕዝብ ሙሉ ለሙሉ ተሳታፊ የሚሆንበት አስተዳደር ለማምጣት የሚታገል ሀይል ወይም ሀይሎች ያስፈልጋሉ።

በሌላ በኩል ፣ ስለ ሕዝብ ብሶት እና ፍላጎት ቆመናል የሚሉ ጎጠኛ ቡድኖች የሚያስተጋቡት ጥያቄ ውሱንነት ያለው ከመሆኑ በላይ እንወክልሀለን የሚሉትን ሕዝብ ብሔራዊ ማንነት በራሳቸው ውሳኔ  የገፈፉት መሆኑን በጥሞና ማስተዋል ይገባል። እነኝህ ሃይሎች ጥያቄያቸው አግባብነት አለው ብንል እንኳ የሚያመለክቱት መፍትሔ ስንኩል መሆኑን መካድ አይቻልም። ሕዝብ ብሔራዊ ማንነቱ ተገፎ በጎጥ መለያ ነፃ ትወጣለህ መባሉን እንዳልተቀበለው ባለፉት አስራስምንት አመታት አይተናል። የአገር ባለቤት ያልሆነ ሕዝብ ፣ ብሔራዊ ማንነት የሌለው ህዝብ ለመፍጠር ተግተው የሠሩት አካሄዳቸው ብዙም አላማረበትም። የሕዝብን ብሔራዊ ማንነት መካድ እና ያንኑ ሕዝብ በጎጥ መለያ ነፃ ላወጣህ ነው ማለት መጎናፀፊያውን ቀምቶ ፣ ክብሩን ገፍፎ ራቁቱን የቆመ ሰው ጥብቆ እስከማሰፋልህ አደባባይ ቆመህ ቆየኝ የማለት ያህል ነው።

በዜግነት አጀንዳ ራቁቱን የቆመ ሰብአዊ ፍጡር የአገር ባለቤትነትን ከተጎናፀፈ ወገን ጋር መቀላቀል ይቸግረዋል። ራዕያቸው አይገናኝም ፣ አጀንዳቸው አይመሳሰልም። ይህ አካሄድ ትግራይን ነፃ አወጣለሁ ብሎ ማልዶ የተነሳውን ወያኔ ዛሬ ምን ፈተና ላይ እንደጣለው ከማንም የተሠወረ አይደለም። እነ መለስ ዜናዊ በወያኔነታቸው የካዱትን ኢትዮጵያዊነት ለትግራይ ሕዝብ ለማውረስ ሲሉ ያላደረጉት የለም። ይሁንና እነሱ ራቁታቸውን ከመቅረታቸው ሌላ አንዲት ጋት እልፍ ማለት አልቻሉም። ዛሬ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን ጋር የሚያናክሳቸውም አውልቀው የወረወሩት መጎናፀፊያ ራቁታቸውን ስላስቀራቸው ብቻ ነው። እነ መለስ ግብግብ የገጠሙት መጎናፀፊያዬን አልገፈፍም ብሎ በፅናት ከቆመ ሕዝብ ጋር ነው። ዛሬ ዛሬ የነመለስ ካድሬዎች ‘መቸ ኢትዮጵያዊ አይደለንም አልን?’ እያሉ በሰነድ ያወጁትን ክህደት በጆሮ ሊያስተባብሉ እየከጀላቸው ነው። ወያኔና ቅጥፈት ቀለባችን ከሆነ አስራ ስምንት አመት ሆነን።

ሃቁ ግን ኢትዮጵያዊነትን አዋርዶ ፣ አጥላልቶ እና በጎጥ መርህ በታኝ የግንጠላ ድንጋጌ አርቅቆ ኢትዮጵያዊነትን መስበክ የሚጣጣም ነገር ካለመሆኑ ላይ ነው።

በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ሳይቀር ታላቅ ዝናን ያተረፉት የአሜሪካው የወቅቱ ፕሬዜደንት ባራክ ሁሴን ኦባማ በምርጫ ወቅት ባሰሙት ንግግር “…ነጭ አሜሪካ ፣ ጥቁር አሜሪካ ፣ ላቲኖ አሜሪካ ፣ ቢጫ አሜሪካ የሚባል ነገር የለም ፤ ያለው አንድ እና አንድ ዩናይትድ ሰቴትስ ኦፍ አሜሪካ ነው” በማለት የአገር ባለቤትነት እና የሕዝብ አንድነት ለአንድ አገር ምን ያህል ዋስትና እንደሆነ አስገንዝበዋል። ሕዝብን በቆዳ ቀለም፣ በቋንቋ ፣

በሀይማኖት እና በጎጥ የሚከፋፍል የፖለቲካ ሀይል የማንም ወዳጅ ፣ የማንም ነፃ አውጭ ሊሆን አይችልም። የአሜሪካ ጥቁር አጅግ አሰቃቂ የፍዳ ዘመን ውስጥ በነበረበት ወቅት መፍትሔው አሜሪካዊነትን መካድ ነው ብሎ አልተነሳም። ዜጎች በማናቸውም ጥያቄ ዙሪያ የሚደርስባቸውን በደል ለማስወገድ ዜግነታቸውን ፣ ማንነታቸውን መካድ አይኖርባቸውም። የኦሮሞ ይሁን የሶማሌ ፣ የትግራይ በሉት የጋምቤላ…ወዘተ፣ ችግር የሚፈታው ፍትሀዊ በሆነ ኢትዮጵያዊ አስተዳደር ብቻ ነው። ይህ አስተዳደር የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ ውጤት ሊሆን እንዲችል መሥራት ግን አንድ ነገር ነው። ፖለቲካው የተነደፈው አንድ ዜጋ በሌላ በራሱ ዜጋ ላይ ባለው ቂም ፣ ጥላቻ እና ድክመት በሚለው ነጥብ ላይ ከሆነ መፍትሔ የሌለው ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ብስለታችንንም ግምት ላይ የሚጥል ይሆናል። ፍትህ ፣ ሰብአዊ ክብር ፣ የኑሮ ዋስትና እና ደህንነት ባንድ አገር ላይ የሚረጋገጡት ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን በማያሻማ መንገድ የሚያረጋግጥ ሕግ ሲኖር ብቻ ነው።

ግባችን ማነጣጠር ያለበት በዚህ ላይ ብቻ መሆን ሲገባው ወርቃማውን ግዜ እና ሀይል የምናባክነው ግን የሞተ ፈረስ በመደብደብ ነው። አልፎ አልፎ እንደምንታዘበው ፖለቲካ ነክ ትችቶች የሚያተኩሩት በነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ሳይሆን ባፈጁ እና ወቅቱ ከሚጠይቀው ፖለቲካዊ እርምጃ አንፃር አንዳችም ፋይዳ በሌላቸው ጉዳዮች ወይም ግለሰቦች ላይ ነው። ትችቶቹ ስሜታዊ ከመሆናቸው የተነሳ በቀል እና ጥላቻ የሚንፀባረቅባቸው ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ በሚያደርገው የነፃነት እንቅስቃሴ ረገድ የኋልዮሽ የሚጎትቱ ናቸው። **ከተጋፈጥነው ጠላት አኳያ ብዙ ስልታዊ እና አጣዳፊ ሥራ ሞልቶ - ተርፎ ሳለ የፖለቲካ ዘልዛላ ሆነናል።** አካሂዳችን ከርሞ ጥጃ ፣ ቢወቅጡት እንቦጭ የሚሉትን እየሆነ ነው። በዱልድም ብዕር እንጨት እንጨት የሚል ሀተታ ስናረቅ መዋል ሙያ የመሰለን ጥቂት አይደለንም።

ተግባራዊ ውጤት በማናቸውም መስክ ለተሰማራ ሰብአዊ ፍጡር ብቃት መመዘኛ ነው። እገሌ ትጉህ ነው ፣ አስተዋይ ነው ፣ ብቃት እና ችሎታ አለው ፣ ሕዝባዊ ነው ወይንም ያገር አለኝታ ነው ወዘተ… ለመባል ጭብጥ ላይ የተመረኮዘ ፣ ውጤት ላይ የተንተራሰ ምስክርነት ይሻል።  የፖለቲካ ድርጅት ፣ የመሪው ወይም ያመራር አካሉ ብቃት የሚለካው ደግሞ አላማን በብዙሀን ሕዝብ ሕሊና ውስጥ ሰርፆ በቁሳዊ ሕይወት ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ከማስቻሉ ላይ ነው። የፖለቲካ ድርጅት ብቃትም ሆነ ትክክለኝነት አመታት በማስቆጠር አይለካም። ያንድ ፖለቲካ ድርጅት ሕዝባዊነት አላማውን ለማሳካት ሲል በከፈለው መስዋዕትነት ልክ ተመጥኖ የሚከፈል የውዳሴ ካሳ አይደለም ፤ **ፖለቲካ የ ጉማ ጥያቄ አይደለም።** ጨዋታው ጥንቁቅ ተጨዋች ይፈልጋል ፤ አላዋቂ የፖለቲካ ተጨዋች እንደ አላዋቂ ሳሚ ‘ምንትስ’ ይለቀልቃል የሚሉት አይነት ነው። ተቀናቃኞች ብሎ በሚጠረጥራቸው ላይ በሆነ ባልሆነው ጭቃ-ጅራፍ ሲመርግ የሚከርም የፖለቲካ ድርጅት ተግባሩ ካላወቂ ሳሚ ጋር ይመሳሰላል።

ወያኔ አገራዊ ራዕይ በነጠፈበት ጎጠኛ ፖለቲካ ኢትዮጵያን በመዳፉ ውስጥ አስገብቷል ፣ ያገሪቱ መሠረታዊ ችግር የሚመነጨው ‘ከብሔረሰብ ልዩነት እና አድልዎ’ ነው በሚል ያንዱን ክልል ሕዝብ በሌላው ላይ በመቀስቀስ ፤ ቅኝ ገዢዎች የተጠቀሙበትን ከፋፍለህ - ሁሉን ረግጠህ ግዛ በሚል ፖሊሲ አገሪቱን በጥፋት በክሏል። አነሳሱ ፣ አካሄዱም ሆነ ግቡ ፀረ-ኢትዮጵያ ነው። ወያኔ በሕዝብ ዘንድ ያለው አመኔታ ተሟጦ በጨዋ ወግ በምርጫ ድምፅ ‘በቃህ’ ቢባልም እንኳ ‘ይሄ የደርግ ፣ የትምክህተኞች ወይም የጠባቦች ሤራ ነው’ በሚል ሥልጣኑን የሕዝብ ደም በማፍሰስ ማቆየት መርጧል። ወያኔ ሰፌ ሱሪ ታጥቆ ሌሎችን በጠባብነት ለመክሰስ ደፍሯል። አስራ ስምንት አመታት ሥልጣን ላይ ቆይቶ ዛሬም ያገሪቱ ችግር የመነጨው ከሌሎች ነው ይለናል። ‘ትምክህተኛ’ ጋዜጠኞችን ፣ አርቲስቶችን ፣ የፖለቲካ ሰዎችን እንደ አውሬ እያሰደደ ግፍ መፈፀሙን ቀጥሏል። ዛሬ አገራችንን የገጠማት ችግር የሚመነጨው ከፖለቲካ አቋሙ እና አደረጃጀት ዕምነቱ መሆኑን ወያኔ መቀበል አይፈልግም። እሱም እንዲህ ማድረጉ - ቀሪው የፖለቲካ ሀይል ይህን ጥፋት በፅናት ለመመከት አለመቻሉ ሁላችንም የሞተ ፈረስ እየደበደብን ነው ያሰኛል። ይህ በመሆኑ የተነሳ ባንድ በኩል የአገራችን ችግር ሁለንተናዊ በሆነ መስክ እጅግ እየተባባሰ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መፍትሄው የዚያኑ ያህል እየተወሳሰበ ሄዷል። ሁሉም የሞተ ፈረስ እየደበደበ ወንዝ መሻገር ይመኛል። ፈረሱ ፍንክች ባይልም መደብደቢያ ጨንገር ግን አልቸገረንም።